አማኑኤል አለማየሁ (ደጀና)

## የውጭ ምንዛሪን ችግርን ለማቅረብ የቀረበ የመወያያ ሃሳብ

እንደሚታወቀው የውጭ ምንዛሬ (Hard currency) የማግኘት ፈተና የሁሉም አዳጊ አገሮች ፈተና ነው፡፡ አገራችንም እጅግ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ እጥረት ከሚታይባቸው አገሮች ውስጥ አንዷ በመሆኗ ምክንያት አገሪቱ ለሚያስፈልጓት ከውጭ በከፍተኛ መጠን ለሚገዙ የፍጆታ እቃዎች እንደ ነዳጅ ለመሳሰሉት እንዲሁም ለግንባታና ለምርት እቃዎች ማስገቢያ ስትቸገር በተደጋጋሚ ይታያል፡፡

ለአብነት እንኳን በከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ተገዝተው አገርቤት የገቡ የማምረቻ እና የግንባታ ማሽነሪዎች መለዋወጫ እቃ ለማግኘት ወደ ከፍተኛ ወረፋ መግባትን ይጠይቃል፡፡

በአንፃሩ እስከ ቅርብ ጊዜ በግል የንግድ ዘርፍ በተሰማራው ማህረሰብ በኩል የሚገቡ ተሽከርካሪዎች እና የተለያዩ የፍጆታ እቃዎች ብዙም ችግር ሳያጋጥማቸው የጥቁር ገበያውን በመጠቀም እጅግ ብዛት ያላቸው ተሽከርካሪዎች፣ መለዋወጫዎች እንዲሁም የፍጆታ እቃዎች ሲያስገባ ይታያል፡፡ በዚህ እንቅስቃሴ ውስጥ አገራችን እያጣች ያለቸውን ከታክስ እና ከተስተካከለ የንግድ እንቅስቀሴ እጦታ ጋር የተገናኙ ችግሮች ወደ ጉን ትተን ላቀደቻቸው የልማት የግንባታ ፕሮጀክቶች ተጠቃሚነት እንኳን ከዚሁ ወደ ጥቁር ገበያ ከሚጎርፈው የውጭ ምንዛሪ ተጠቃሚ ልትሆን አልቻለችም፡፡ ስለዚህ የዚህ አጭር የመነጋገርያ መነሻ ሃሳብ ዋናው ነጠብ አገራችን እንዴት ወደ ጥቁር ገበያ ከሚጎርፈው የውጭ ምንዛሪ ተጠቃሚ ትሆናች የሚል ጠቋሚ መፍትሄ ለማቅረብ ነው፡፡

1. የጥቁር ገበያ የገንዘብ እንቅስቃሴ መጠን ግምቶች

እስከ ቅርብ ድረስ በነበረው አሰራር አንድ የግል ተሽከርካሪ በህጋዊ መንገድ ሲመጣ በባንክ የሚፈቀድለት የውጭ ምንዛሪ መጠን አማካይ ከ200.00 የአሜሪካን ዶላር የማይበልጥ ነው፡፡ ነገር ግን የአንድ መኪና አማካይ የመግዣ ዋጋው 25,000.00 የአሜሪካን ዶላር ነው፡፡ በመሆኑም አንድ መኪና ለማስመጣት ከባንክ በተፈቀደ ህጋዊ ገንዘብ 200 ከመግዣው ሲቀነስ 24,800.00 የአሜሪካ ዶላር ወይ ከጥቁር ገበያ ወይም ህጋዊ ካልሆነ ሃዋላ መገኘት አለበት ማለት ነው፡፡ በእኛ አገር ሁኔታ ሲታይ በአብዛኛው ከጥቁር ገበያ ይገኛል ማለት ነው፡፡ በቀን በአማካይ 100 መኪኖች እያገቡ ከሆነ 2,480,000 የአሜሪካን ዶላር ይወጣል ማለት ነው *(መጠናት እንዳለበት ታሳቢ በማድረግ)*፡፡ በተመሳሳይ መንገድ እጅግ ከፍተኛ መጠን ያላቸው፡-

1. አልባሳት
2. የምግብ ሸቀጣሸቀጦች
3. የመገልገያ ቁሳቁሶች
4. የኢንዱስትሪ ግብአቶች
5. የግንባታ እቃዎችና ማሽኖች
6. ኬሚካሎች ወዘተ

ከዚሁ ከጥቁር ገበያ ተቋዳሽ በመሆን በየቀኑ ይገባሉ፡፡ በአንፃሩ በህጋዊ የባንክ ፍቃድ (LC, CAD or TT) እጅግ ዝቅተኛ መጠን ያለው ንብረት የሚገባ ሲሆን የሚያንቀሳቀሰው የውጭ ምንዛሪ መጠንም ዝቅተኛ ነው (ዝርዝር ቁጥሮችን ለጥናት በመተው)

በመሆኑም በአገር ውስጥ እየተፈጠረ ባለው የውጭ ምንዛሪ እጥረት ሳቢያ የመንግስትና የህዝብ ከፍተኛ ጠቀሜታ ያላቸው ፕሮጀክቶች ይጓተታሉ ሀገራችን ለውጭ ብድር መክፈያ የሚስፈልጋትን የውጭ ምንዛሪ መጠን ታጣለች (ያጥራታል) በተጨማሪም ቀጣይነት ያላቸው ፕሮጀክቶች የእያንዳንዱን ዜጋ ሂወት ማሻሻል ይቻል የነበረውን ጊዜ እያራዘመ በውጭ ምንዛሪ ላይ የተመሰረቱ ብሮጀክቶች የህዝብ ችግር ሳይፈቱ እንዲጓተቱ ምክንያት ይሆናል፡፡

2. የጥቁር ገበያው የውጭ ምንዛሪ ምንጮች፡-

የጥቁር ገበያው የሚያገኛቸው የውጭ ምንዛሪ ምንጮች ከብዙዎቹ በጥቂቱ ፡ -

I. በውጭ ከሚኖሩ ኢትዮጲያውያን ከሚላክ ገንዘብ (Remitance)
II. አገር ጎብኝዎች ይዘውት ከሚመጡ

III. በውጭ ምንዛሪ ተካፋይ ከሆኑ የዲፕሎማቲክ ማህበረሰብ እና ሌሎችም ሲሆኑ በተለይ በተራ ቁጥር አንድ እና ሁለት የተጠቀሱት ከፍተኛውን መጠን ይይዛሉ፡፡

በውጭ አገር ከሚኖሩ ወደ ሶስት ሚሊዮን ከሚጠጉ ኢትዮጵየውያን እና ትውልደ ኢትዮጲያውያን ውስጥ በትንሹ 30% የሚሆኑት ቤተሰቦቻቸውን በተለያየ ወቅት በገንዘብ ይደጉማሉ ቀሪዎቹ አልፎ አልፎ ገንዘብ የሚልኩ ቢሆንም 30% ግን በቋሚነት የሚደጉሞ ናቸው፡፡ ከነዚሁ 30% ውስጥ በህጋዊ መንገድ የሚልኩት ከ40% የሚመልጡ አይሆኑም (መጠናት ያለበት ሆኖ)

በመሆኑም ቀሪዎቹ 60% በየአካባቢያቸው ባሉ ገንዘብ አስተላላፊዎች ወይም ወደ አገር ቤት በሚመጡ ዘመድ ጓደኛ እና የሚያውቁት ሰው አማካኝነት ለቤተሰባቸው ያደርሳሉ፡፡ ገንዘቡ የደረሳቸው ቤተሰቦች በግልፅ በሚታወቁ የውጭ ምንዛሪ ቀያሪዎች (money exchanges) አማካኝነት ወደ ጥቁር ገበያው ፈሰስ (inject) ያደርጋሉ፡፡

በሁለተኛ ላይ የጠቀስኳቸው ቁጥራቸው እጅግ ከፍተኛ የሆኑት አገር ጎብኝዎች የኮንፈረንስ ተሳታፊዎች እዲሁም በተለያየ የስራ ምክንያት ወደ ኢትዮጵያ የሚገቡ ቱሪስቶች ይዘውት የሚገቡትን የውጭ ምንዛሪ ወደ ጥቁር ገበያ ወስደው በመመንዘር ለተለያዩ አገልግሎት እና እቃዎች መግዣ ያውሉታል፡፡ እነዚህ ቱሪስቶች መጠኑ ቀላል የማይባል የስጦታ እቃዎች፣ የከበሩ ድንጋዮችን፣ የአርት ውጤቶችን በጥቁር ገበያ በመነዘሩት ብር አማኝነት ገዝተውት ይሄዳሉ፡፡

በመሆኑም ከላይ በጠቀስኳቸው እና በጥናት ሊካተቱ በሚገባቸው መንገዶች አማካኝነት እጅግ ከፍተኛ መጠን ያለው የውጭ ምንዛሪ አገሪቷ ሳትጠቀምበት፤ በቅርብ ጊዜያት እንኳዋን በተደጋጋሚ እንደምንሰማው በህገወጥ መንገድ አገር አቋርጦ ይላካል፡፡

## <u>የመፍትሄ ሃሳብ፡ -</u>

### ሀ. የተወሰኑ የውጭ ገንዘቦችን እንደ አማራጭ መገበያያ ለተመረጡ የግብይት ዘርፎች መፍቀድ፡-

ይህ ሃሳብ በብዙ አገሮች ተግባር ላይ የዋለ እና እየዋለ ያለ ሲሆን በተለይ ኢኮኖሚያቸው በማኑፋክቸሪንግ ላይ ላለተመሰረቱ አገሮች እጅግ አጋዥ ሆኖ ይታያል፡፡ ለምሳሌ በተባበሩት አረብ ኤምሬትስ በማንኛውም የውጭ ምንዛሪ በቀኑ የምንዛሪ ስሌት መሰረት አገልግሎት ማግኘት የተለመደ ነው፡፤

ዚምባቡዌ አጋጥሟት የነበረውን ከፍተኛ ዋጋ ግሽበት (hyperinflation) ለመቋቋም ከተጠቀመችበት አንደኛው መፍትሄ የአሜሪካ ዶላርን እና የደቡብ አፍረካ ራንድ እንደ ተለዋጭ (alternete) ምንዛሪ ገበያ ውስጥ ማዋል ነበር፡፡ በመሆኑም እንደ UAE አይነት አገሮች የውጭ ምንዛሪ እጥረት ሲያጋጥማቸው አይስተዋልም፡፡

ከላይ የተጠቀሰውን ሃሳብ ተግባር ላይ ለማዋል በተለይ በተመረጡ የንግድ ጠቀሜታ ያለው ይመስለኛል

1. የንግድ ዘርፉ በተለይ ኢትዮጲያ ወደውጭ በምትልካቸው እቃዎች ላይ የሚያተኩር ቢሆን እና የገንዘብ መጠኑም እስከ 10,000 USD ቢገደብ (ገደቡ የሚያስፈልገው ከአለማቀፍ የህገወጥ የገንዘብ ዝውውር ጋር ታሳቢ በማድረግ ነው)
2. በተፈቀደው ንግድ ዘርፍ ላይ የሚሰማሩ አካላት በውጭ ምንዛሪ ለሚደረግ ግብይት ለዚሁ ተብሎ በገቢዎች እና ጉምሩክ ባለስልጣንና በብሄራዊ ባንክ እውቅና ባለውና በውጭ ምንዛሪ ግብይት የሚያገለግል ደረሰኝ የመቁረጥ፣
3. በውጭ ምንዛሪ ግብይት ደረሰኝ የተሰበሰበን የውጭ ምንዛሪ የባንክ ሂሳብ የመክፈት ልዮ ፈቃድ ቢሰጣቸው እና ይህ የሚያከማቹት የውጭ ምንዛሪ እቃ ከውጭ ለማስመጣት፣ ለባነኮች ተደራድረው የመሸጥ እና የውጭ ምንዛሪ የባንክ ሂሳብ ላላቸው አስመጭዎች በድርድር ሽጠው እንዲጠቀሙ ፈቃድ ቢሰጣቸው የውጭ ምንዛሪ የማከማቸት ፍላጎት ይኖራቸዋል፡፡
4. ይህ በውጭ ምንዛሪ የባንክ ሂሳብ ውስጥ የሚያስቀምጡት ገንዘብ በደረሰኝ የሚሰበሰብ በመሆኑ ኦዲት የሚደረግ እና ተፈላጊውን (ህጉ የሚጠይቀውን የገቢ ግብር ከ ተ.እ.ታ. ውጭ) የሚከፍሉበት ቢሆን ሰብሳቢዎችንም ገዥዎችንም ያበረታታል፡፡

<u>ተደራሽ ጥቅሞች</u>

1. ገዥው፡-
   አንድ ቱሪስትም ይሁን እቃ ገዝቶ ወደ ውጭ መላክ ወይንም መውሰድ የሚፈልግ ሰው በውጭ ምንዛሪ የያዘውን ገንዘብ ወደ ጥቁር ገበያ ወስዶ ከዘረዘረ በኋላ የሚፈልገውን እቃ ይገዛበታል ይህ ደግሞ አገሪቱን የውጭ ምንዛሪ ያሳጣታል፡፡ እቃ ገዥውም ቢሆን በብር የገዛውን እቃ ወደ ውጭ መላክም ይሆን ይዞ ሲሄድ ልዩ መብት (ፈቃድ) ከሌለው በስተቀር ይዞ ለመውጣት ወይም ለመላክ ይቸገራል፡፡ በባንክ ፈቃድ ብቻ ካልሆነ ከተባለም ከ1% - 2% ለውጭ ባንኮች የአገልግሎት ክፍያዎችን አለአግባብ መክፈልን ከማስከተሉም አልፎ ወደ

ተራዘመ ቢሮክራሲ ያስገባል፡፡ ስለሆነም በድብቅ ወይም በኮንትሮባድ እቃው እንዲወጣ ያበረታታል፡፡ በዚህ ሂደት ውስጥ ከኮንትሮባንዲስቱ ውጭ ማንም ተጠቃሚ የለም፡፡

በመሆኑም የከበሩ ድንጋይ፣ የስጦታ እቃዎች፣ የስእልና የአርት ውጤቶች፣ ቡና፣ቅመማቅመሞች እና የመሳሰሉት ህጋዊ የውጭ ምንዛሪ ደረሰኝ ተቆርጦላቸው እና በመጠን ተገድበው እንዲሸጡ ቢፈቀድና ይዞ የሚሄደው ሰው ወይም የጉምሩክ አስተላላፊው አንድ ደረሰኝ ኮፒ በሚወጣበት የጉሞሩክ ኬላ በመተው እና አንድ ኦርጅና በእጅ በመያዝ የገዛውን እቃ ይዞ እንዲወጣ የሚያስችል አሰራር ቢኖር ሃገሪቷም ሻጩም እቃ ይዞ የሚወጣውም ሰው ተጠቃሚዎች ይሆናሉ፡፡

2. **ሻጭ**

   እቃ የሚሸጠው ባለተቋም ህጋዊ የውጭ ምንዛሪ ደረሰኝ እንዲቆርጥ አስገዳጅ ህግ ቢኖር እንዲሁም በደረሰኝ ቆርጦ የሰበሰበውን የውጭ ምንዛሪ በማንኛውም ባንክ በውጭ ምንዛሪ አካውንት ከፍቶ እንዲያጠራቅም እና ያከማቸውን የውጭ ምንዛሪ ለማስመጣት አግልግሎት እንዲጠቀምበት መፍቀድ ሻጭ የውጭ ምንዛሪ ክምችት ፍላጎት እንዲኖረው እንዲሁም ተጠቃሚ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡ በዚህም ምክንት የውጭ ምንዛሪ ችግር እንዳይኖረው ያደርጋል፡፡

3. ተለዋጭ የግብየት ገንዘብ መኖሩ በመጠኑም ቢሆን የዋጋ ግሽበትን ለመቆጣጠር ማገዝ የሚቻልበት ሁኔታ አለ፡፡ በውጭ ምንዛሪ ተገዝተው ወደ ውጭ የሚላኩት ሸቀጦች፤ የውጭ ምንዛሪ የግብይት አማራጭ ከሌለ በአገርውስጥ ገንዘብ (soft currency) ስለሚገበዩ የብር ዝውውር መጠን ላይ ጭማሪ ማሳየታቸው አይቀርም፡፡ በአንፃሩ በተፈቀደ የውጭ ምንዛሪ በኩል ግብይቱ የሚፈፀም ከሆነ ግን የብር ዝውውር መጠኑን በመቀነስ የዋጋ ግሽበትን በአንድ መንገድ (by one factor) ለመቀነስ ያግዛል፡፡
4. በውጭ ምንዛሪ ግብይት ውስጥ ቢካተቱ ጥሩ ይሆናል የምላቸው ዘርፎች፡-
   I. የከበሩ ድንጋዮች
   II. የከበሩ የብረት ውጤቶች
   III. ባህላዊ እና ዘመናዊ ስጦታ እቃዎች
   IV. የጌጣጌጥ ምርቶች
   V. የስነጥበብ ውጤቶች (ስእሎች ቅርፃቅርፆች)
   VI. የሆቴል አገልግሎቶች
   VII. ባጠቃላይ ሃገሪቷ ለወጪ ንግድ የምትጠቀምባቸው የግብርና እና የኢንዲስትሪ ውጤቶች ሆነው ዋጋቸውና መጠናቸው በህግ ቢገደብ

**ለ. የጥቁር ገበያ ምንዛሪዎችን ህጋዊ ስለማድረግ፡-**

እንደሚታወቀው የጥቁር ገበያው በአመት በቢልዮኖች የሚቆጠር የውጭ ምንዛሪ ያንቀሳቅሳል፡፡ ከላይ ለአብነት የጠቀስኩት የመኪና ግዥ ዋናው ሞተሩ የጥቁር ገበያው ነው፡፡ በመሆኑም ከጥቁር ገበያ ሻጭና ገዥዎች የሚደረገው ግብግብ እጅግ አስልቺ ከመሆኑም ባሻገር ማቆሚያ ያለውም አይደለም፡፡

በዚህ የመፍትሄ ሃሳብ ውስጥ የጥቁር ገበያ መንዛሪዎችን ህጋዊ ፈቃድ አውጥተው እንዲሰሩ የሚደረግ ህጋዊ ማእቀፍ መፍጠር የውጭ ምንዛሪ የመሰበሰብ አቅማችን እጅግ አስፈላጊ ነው የሚል እምነት አለኝ፡፡

**I. ህጋዊ ሊሆኑ የሚችሉበት እና ለታሰብበት የሚገባው መነሻ**

የጥቁር ገበያ መንዛሪዎች ህጋዊ እንዲሆኑ በሚታሰብበት ወቅት ለምን ወደ ህጋዊ የምዛሪ ማእቀፍ ውስጥ እንደሚገቡ እና ምን ምን ዓይነት ጥቅም ሊያገኙ እንደሚችሉ ማሰቡ እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡

ሀ) ህጋዊ ሆነው መስራታቸው ሃገሪቷ ያወጣችውን (እየሰራ ያለውን) የውጭ ምንዛሪ የመያዝ እና የመዘርዘር አዋጅን (መመርያን፣ ደንብን) ማሻሻል ያስፈልጋል፡፡ ይህ በሚደረግበት ወቅት፣ የውጭ ምዛሪ መንዛሪዎች ህጋዊ ሆነው የመስራት መብት የሚሰጥ ህግ ወይም መመርያ መውጣት አለበት፡፡

ለ) የሚሰበሰቡትን የውጭ ምንዛሪ ለባንኮች፣ ላስመጪዎች እንዲሁመ ለመንግስት እንዲሸጡ ቢደረግ እና በውጭ ምንዛሪ ሰብሳቢዎች እና በበድሄራዊ ባንክ መካከል ጥብቅ እና ሚስጥራዊ እንዲሁም ከእያንዳንዱ አቅራቢ ጋር ብቻ በሚደረግ የመሸጫ ውል ቢታሰር፡፡ ይህ የመሸጫ ውል ሚስጥርን በጥብቅ የመጠበቅ ስምምነት (nondisclosure agreement) የተደገፈ እና አንዱ አቅራቢ ለባንክ ያቀረበበትን ዋጋ በሚስጥራዊነት የሚጠበቅበት አሰራር ቢኖር፡፡ የዚህ ጥቅም ለምሳሌ ብሄራዊ ባንክ ለአቅራቢዎች 5% -10% በሚኖር ጭማሪ ተስማምቶ ቢገዛ የውጭ ምንዛሪው የተገዛበት ዋጋ የሚቀጥለው የውጭ ምንዛሪ አቅርቦት ዋጋ ላይ ጫና ሊፈጥር ስለሚችል ጥንቃቄ ስለሚፈጥር ነው፡፡

በዚህም መሰረት በህገወጥ መንገድ ከጥቁር ገበያ ከመንግስት (ብሄራዊ ባንክ ቁጥጥር ውጭ ሊንቀሳቀስም ይሁን ውደውጭ ሊወጣ የሚችለውን የውጭ ምንዛሪ በከፍተኛ ደረጃ ሊያስተካክል) ሊቀንስ ችላል፡፡ በዚሁም መሰረት አገራችን በትንሹ በዓመት ቢልዮኖች ዶላር ማግኘት ትችላለች የሚል ግምት አለኝ፡፡




**የህጋዊ መንዛሪዎች (money exchange) ጥቅማ ጥቅሞች**

1. በህጋዊነት በባንክ የውጭ ምንዛሪ አካውንት ከፍተው እንዲያጠራቅሙ ማድረግ ቢችሉ
2. ያጠራቀሙትን የውጭ ምንዛሪ ከባንኮች ጋር ተደራድረው የመሸጥ መብት ቢያገኙ
3. ያጠራቀሙትን የውጭ ምንዛሪ የአስመጭነት ፈቃድ ካላቸው እቃ እንዲያስመጡበት ቢደረግ
4. ከአስመጭዎች ጋር ተደራድረው ያከማቹትን የውጭ ምንዛሪ ለአስመጪዎች ሽጠው ቢጠቀሙ

ከላይ የጠቀስኳቸው ጥቅማጥቅሞች የሚገኙባቸው መንገዶች የውጭ አገር ገንዘብ መንዛሪዎችን በጥቅም እና በህጋዊነት እንዲሰሩ ስለሚያበረታታቸው ለሃገሪቱ ተፈላጊውን የውጭ ምንዛሪ እንዲያጠራቅሙ ያደርጋቸዋል፡፡

**በዚህ የውጭ ምንዛሪ ግብይት ውስጥ ሊሳተፉ የሚችሉ አካላት**

1. ህጋዊ ንግድ ፈቃድ ያላቸውና በውጭ ምንዛሪ ሊሸጥ በሚችል እቃ ግብይት ውስጥ የተሰማሩ
2. ህጋዊ የአስመጪነት ፈቃድ ያላቸውና የውጭ ምንዛሪ የባነክ ሂሳብ የከፈቱ
3. ህጋዊ የውጭ ምንዛሪ ለዋጮች (foreign currency exchanges)
4. የንግድ ባነኮች
5. ብሄራዊ ባነክ

አመሰግናለሁ